# ከቆሎ ተማሪነት እስከ አምባሳደርነት - የሃዲስ አለማየሁ አጭር የሕይወት ታሪክ

ፀሐፊ - ጌታ በለጠ ( ደብረ ማርቆስ፣ ጎጃም)

..............................................................................................




ዛሬ ጥቅምት 7 ቀን ነው። ከዛሬ ብዙ ዓመታት በፊት (ጥቅምት 7 ቀን 1902 ዓ/ም) በቀድሞው ጎጃም ክፍለ ሃገር፣ ደብረ ማርቆስ አውራጃ፣ ጎዛምን ወረዳ ውስጥ እንዶዳም ኪዳነ ምሕረት የሥነ ፅሑፍ አድባር፣ የሐገር አለኝታ የሆኑት ታላቁ ደራሲ፣ አርበኛ፣መምህር እና ዲፕማት ሃዲስ አለማየሁ ምድርን ተቀላቀሉ።ይኼንን ቀን በማስመልከት የደራሲ፣ አርበኛ፣ መምህር እና ዲፕሎማት ሃዲስ አለማየሁን አጭር የሕይወት ጉዞ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

የሃዲስ ዓለማየሁ አባት (አለማየሁ ሰለሞን) ትውልድ አገራቸው ጎጃም ውስጥ ደብረ ኤልያስ ነው።አለማየሁ ሰለሞን የቤተ ክህነት ሰው በመሆናቸው ከትውልድ መንደራቸው ወደ ጎዛምን ወረዳ እንዶዳም ኪዳነ ምህረት በመኼድ የቤተ ክርስቲያኗ አገልጋይ ሆኑ። በእንዶዳም ኪዳነ ምሕረት አንድ የታወቁ አለሙ ሥዩም የተባሉ የዜማ መምህር ነበሩ። አለሙ ሥዩም ደስታ የምትባል ሴት ልጅ ወልደዋል። ለአገልግሎት አካባቢቸውን ለቅቀው የኼዱት አለማየሁ ሰለሞን የአለሙ ሥዩምን ልጅ (ደስታን) አገቡ እና ወንድ ልጅ ወለዱ። ሥሙንም ሃዲስ አለማየሁ አሉት። በኋላ አለማየሁ ሰለሞን የተሻለ ሥራ ፍለጋ

እንደዳም ኪዳነ ምሕረትን ለቅቀው ወደ ኢሊባቡር ሲኼዱ ወይዘሮ ደስታ አለሙ ህፃኑን (ሃዲስ አለማየሁን) ይዘው ከአባታቸው ቤት መቀመጥ ጀመሩ። ሃዲስም እዚያ ከአያቱ ቤት ዳዊት እና ዜማ እና ድጓ ተምረው አጠናቀቁ።

ሃዲስ ዕድሜያቸው ከፍ ሲል ቅኔ ለመማር ወደ አባታቸው መንደር ደብረ ኤልያስ አቀኑ። ደብረ ኤልያስ ውስጥ ገብረሥላሴ ከሚባሉ የቅኔ መምህር ላይ ቅኔ መማር ጀመሩ።ሃዲስ አለማየሁ ከትቂት ጊዜ ከትቂት ጓደኞች በኋላ ከደብረ ኤልያስ ወደ ደብረ ወርቅ ማርያም በመኼድ ከመምህር አለቃ ይሂይስ ዘንድ ተጨማሪ የቅኔ ትምህርት መማር ጀምረው ነበር። መምህር አለቃ ይሂይስ የነ ሃዲስን ከደብረ ኤልያስ መምጣት ባወቁ ጊዜ ወደ ዲማ ጊዮርጊስ እንዲኼዱ አደረጓቸው። የቆሎ ተማሪ ህይወት ነውና ሃዲስ እና ጓደኞቹ ደብረ ወርቅ ማርያምን ተሰናብተው ወደ ታላቁ የቅኔ ትምህርት ቤት ዲማ ጊዮርስ አመሩ። ሃዲስ አለማየሁ በዲማ ጊዮርጊስ አለቃ በላይ ከሚባሉት መምህር የውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ትምህርት መማር ይጀምራሉ።

ሃዲስ አለማየሁ የጀመሩትን የውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ትምህርት ሳይጨርሱ መምህር አለቃ በላይ ከዲማ ማሕበረሰብ ጋር ይጣላሉ። መምህር አለቃ በላይ ዲማ ጊዮርጊስን በመተው ወደ ሰላሌ ሲኼዱ እነ ሃዲስ አለማየሁ መምህራቸውን ተከትለው ሰላሌ ገቡ። ከትቂት ወራት በኋላ መምህር አለቃ በላይ ሹመት ተሰጥተው ወደ ደብረ ብርሃን ሲኼዱ እነ ሃዲስ አለማየሁ በእግር ተጉዘው አዲስ አበባ ውስጥ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ገቡ። ከእለታት በአንዱ የሃዲስ ህይወት የሚለውጥ ክስተት ተፈጠረ። ሃዲስ አለማየሁ እና ጓደኞቹ በአዲስ አበባ ጎዳና ሲዘዋወሩ አንድ ባለሱቅ ያገኛሉ። ሱቁ የዳቦ መሸጫ ነው። ባለሱቁ የተዋቂው የቲያትር ደራሲው እና ባለቅኔው ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ወንድም አያሌው ንጉሴ ነበር። አያሌው ንጉሴ የጎጃም፣ ደብረ ኤልያስ ተወላጅ ነው። አያሌው ንጉሴ እነ ሃዲስን ዘመናዊ ትምህርት እንዲማሩ ሲጠይቃቸው ሃዲስ አለማየሁ " ዘመናዊ ትምህርት መማር ሐይማኖቴን ያስለውጠኛል" ብለው እምቢ ሲሉ ሌሎች ፍቃዳቸውን ሰጡ። አያሌው ንጉሴ ሃዲስ አለማየሁን "ቄስ ባድማ" በሚባል ሰው አማካኝነት ዘመናዊ ትምህርት ሐይማኖትን እንደማያስለውጥ እንዲያሳምኑ ካደረገ በኋላ የስዊድን ምስዮን ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲመዘገብ አደረገ።

እነ ሃዲስ አለማየሁ በዚህ ትምህርት ቤት አንድ ዓመት ከስድስት ወር ከተማሩ በኋላ ወደ " ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት" ገብተው ለመማር ክፍያ ያስፈልግ ነበር። በዚህ ጊዜ

አያሌው ንጉሴ የእነ ሃዲስን ትምህርት በተመለከተ ሊረዳው የሚችል ሰው ሲያስብ የጎጃሙ ራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት ትዝ አለው። አያለው ንጉሴ የራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት እንደራሴ ለነበረው ለቀኛዝማች ይመር ጉዳዩን በደብዳቤ አሳወቀ። ቀኛዝማች ይመር ከራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት ጋር ተመካክሮ ራስ ኃይሉ ፍቃዳቸውን በመስጠታቸው እነ ሃዲስ በ "ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት" መግባት ቻሉ። አሁን ሃዲስ "የተፈሪ መኮነን ትምህርት ቤት" ጎበዝ ተማሪ ሆነዋል። ሃዲስ የሥነ ፅሑፍ መክሊታቸውን ያገኙት እና በተግባር ያዳበሩት በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ነው። ጃንሆይ ባሉበት ልዩ ልዩ ሥራዎችን አቅርበዋል።

በትምህት ቤቱ የትምህርት መዝጊያ ወቅት ተማሪዎች የሥነ ፅሑፍ ሥራ ያቀርቡ ስለነበረ ሃዲስ አለማየሁ "ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ" የተሰኘ ቲያትር ፅፈው ለማቅረብ ቢያመለክቱም ቋንቋውን የማይረዱ የውጭ ዜጎች በፕሮግራሙ ስለሚገኙ መውረብ የለበትም በሚል ምክንያት ሳይቀርብ ቀረ።

በ1923 ዓ/ም ሃዲስ አለማየሁ የ5ኛ ክፍል ትምህርት እንደጨረሱ በፈተና ወቅት ተማሪዎች በመምህራ ላይ አመፅ ጠርተው እና አድማ ይዘው ስለነበረ በአዳሪነት (በነዋሪነት) ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች ከግቢ ወጥተው ተመላላሽ ተማሪ ሆነው እንዲማሩ ተወሰነ። ሃዲስ አለማየሁ ከተማ ዘመድ የሌላቸው በመሆኑ ትምህርታቸውን ሊያቋርጡ ችለዋል።ሃዲስ አለማየሁ ከዚህ በኋላ ወደ ሥራ ዓለም ነው የገቡት።

ሃዲስ አለማየሁ እና የተወሰኑ ጓደኞች በድብቅ አንድ ማህበር አቋቁመው የማህበሩ መሪም ሃዲስ ሆነው ተመርጠው ነበር። በወቅቱ የነበረው ፖለቲካ ስለማይፈቅድ እንጅ ማህበሩ ዓላማው የሐገሪቱን ልማት ማፋጠን ላይ የተመሰረተ ነበር። እነ ሃዲስ ያቋቋሙትን ማህበር ሊደግፍ የሚችል ገንዘብ ማግኘት አልቻሉም።ወዲያውኑ አንድ ሃሳብ መጣላቸው። ይኼውም በትምህርት ቤት መዝጊያ ወቅት ሃዲስ ሊያቀርቡት የነበረው እና በክልከላ ምክንያት ሳይቀርብ የቀረውን "ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ"የተሰኘ ቲያትር በማቅረብ በሚገኘው ገንዘብ ማህበሩን መደገፍ የሚል ነበር።

ሃዲስ አለማየሁ የቲያትር ድርሰቱን በወቅቱ የሐገር ግዛት ሚኒስትር ለነበሩት ደጃዝማች ወልደፃዲቅ አሳይተው ሚኒስትር ስለወደዱት መጀመሪያ ጳጉሜ 1 ቀን 1923 ዓ/ም፣ ለሁለተኛ ጊዜ ጥር 8 ቀን 1924 ዓ/ም ከተማው ውስጥ በሚገኝ ሆቴል ውስጥ መኳንንት፣

መሳፍንቱ እና እነ ሃዲስ አቋቁመውት የነበረው ድብቅ ማህበር አባላት ባሉበት ሊታይ ችሏል። ከትያርትሩ መግቢያ የተገኘው ገንዘብ ብዙ ነበር።ትያትሩ እጅግ በጣም መወደዱን የሰሙት ኃይለሥላሴ ልጃቸውን (ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን) ሲድሩ በሚድሩበት ሰዓት የእነ ሃዲስ አለማየሁ ትያትር እንዲቀርብ አዘዙ። ነገር ግን " ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ" የተሰኘው ትያትር ለሰርግ የሚሆን አለመሆኑን ጠቅሰው ቀኝጌታ ዮፍታሔ ንጉሴ በደራሲነት የተሳተፉበት "ሆድ አምላኩ" የተሰኘ ትያትር አቀረቡ። በዚህ ትያትር እነ ጃንሆይ ደስ አላቸው።

ሃዲስ አለማየሁ የአምስትኛ ክፍል ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ቀድመው ተምረውበት ከነበረው የስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት በመምህርነት ሙያ ሥራ ጀመሩ። በዚያን ወቅት የኢንግሊዝ መንግስት በጎጃም፣ ዳንግላ ከተማ ውስጥ የቆንስላ ፅህፈት ቤት ከፍቶ ስለነበር ለግምሩክ መስሪያ ቤት ሰራተኛ የሚሆን የተማረ ሰው አስፈለገ። ሃዲስ ተመርጠው ወደ ዳንግላ በመኼድ የቆንስላ ፅህፈት ቤቱ ውስጥ የግምሩክ ተቆጣጣሪ ሆኑ። በ1926 ዓ/ም በግልጽ ባልታወቀ ምክንያት የዳንግላው ቆንስላ ፅህፈት ቤት ተዘጋ። ቆንስላው ትምህርት ቤት ሆኖ እንዲቀጥል ስለተፈለገ ሃዲስ አለማየሁ እዚያው ቦታ ትምህርት ቤት የማቋቋሙን ኃላፊነት ወስደው እዚያው መምህር እና ዳይሬክተር ሆኑ።

በ1927 ዓ/ምን ሃዲስ አለማየሁ ከዳንግላ ወደ ደብረ ማርቆስ ተዛውረው ተራ መመህር ሆኑ። ሃዲስ የመምህርነት ሥራቸውን እየሰሩ እንዳለ ከጣሊያን ጋር ያለው ጦርነት የማይቀር መሆኑን የተገነዘቡት ፊታውራሪ  ወልደ ጊዮርጊስ ተድላ (በወቅቱ ለጎጃም ትምህርት ክፍል ኃላፊ የነበሩ) ሃዲስን አንድ ትዕዛዝ አዘዙ። ትዕዛዙ በቲያትር ሕዝቡን ለጦርነት መቀስቀስ ነበር። ሃዲስ አለማየሁ "የኢትዮጵያ እና የጣሊያን የጦርነት በአድዋ" የተሰኘ ፉከራና ቀራርቶ ያጀበው ቲያትር በመድረስ ሕዝቡን ከማነሳሳት ባለፈ በወቅቱ የጎጃም ገዥ ከነበሩት ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ጋር በመሆን ወደ ግንባር ዘመቱ። በግንባር ብዙ ደክመዋል። ጥረዋል።

ይሁን እንጅ በጣሊያን እጅ ወድቀው የካቲት መግቢያ ላይ 1929 ዓ/ም ወደ ጣሊያን በግዞት ተላኩ። የአርበኝነት እና የግዞት ዘመናቸውን ለማወቅ "ትዝታ" የሚለውን መፅሐፍ ማንበብ ይመከራል። ከስድስት ዓመታት የግዞት ቆይታ በኋላ ኅዳር 10 ቀን 1936 ዓ/ም ሃዲስ አለማየሁ አዲስ አበባ ገቡ። ከስዴት መልስ በፅህፈት ሚኒስትር ስር በሚተዳደር "የጋዜጣው ክፍል" ውስጥ እንዲሰሩ ተደረገ። ከትቂት የአገልግሎት ጊዜ በኋላ በ1937 ዓ/ም

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መስሪያ ቤትን እንዲመሩ ተደረጉ። በዚሁ ዓመት መጋቢት ላይ በእየሩሳሌም የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው ተመደቡ።ይኼ ወይዘሮ ክበበፀሀይ በላይ ጋር አገናኛቸው። ከወይዘሮዋ ምንም እንኳ በልጅ ባይታደሉም የ15 ዓመታት ትዳር ነበራቸው። በኋላ ወይዘሮዋ ሞተች። ሃዲስ ከሚስታቸው ሞት በኋላ አላገቡም።

ነሐሴ 8 ቀን 1939 ዓ/ም በዋሽንግተን የግርማዊነታቸው ሌጋሲዮን ዋና ፀሐፊ ሆነው ተመደቡ። ከዚህ ሥራ ጎን ለጎን  በተመድ "ትንሹ ጠቅላላ ጉባኤ" ተሳታፊ ለመሆን በቅተው ነበር። በጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በማታው መርሐ ግብር  አለም አቀፍ ሕግ (International Law) ተምረዋል። ሃዲስ ከዋሽንግተን ተመልሰው  ከታህሳስ 10 ቀን 1943 እስከ ሐምሌ 1949 ዓ/ም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር  ዋና ዳይሬክተር በመሆን ሐገራቸዉን አገልግለዋል። ሐምሌ 19 ቀን 1949 ዓ/ም በተባበሩት መንግስታት ማህበር በአምባሳደርነት ማዕረግ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዋና መልዕክተኛ ተብለው ተሾሙ። ሰኔ 3 ቀን 1952 ዓ/ም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴታ ተብለው አዲስ አበባ ተመለሱ። በኋላም የካቲት 2 ቀን 1953 የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴታ ሆነው ተመርጠዋል። ከሐምሌ 26 ቀን 1953 ዓ/ም እስከ 1958 ዓ/ም በለንደን የግርማዊነታቸው ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር እና ልዩ መልዕክተኛ በመሆን አገልግለዋል። በግንቦት 3 ቀን 1958 ዓ/ም የፕላናን ልማት ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ። በኋላ በ 1961 ዓ/ም ከመንግስት የሥራ አስፈፃሚነት እና በ1966 ዓ/ም ከሕግ መወሰኛ ምክር ቤት  በ1966 ዓ/ም ለቅቀው ወጡ። የደርግ መንግስት ስልጣን እንደያዘ ሃዲስ አለማየሁን ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆኑ ዘንድ ጠይቋቸው ነበር። ሃዲስ አለማየሁም "እስኪ ፖሊሲያችሁን አሳዩኝ" ቢሏቸው ደርጎች ወደ ሥራ ከገባህ በኋላ ይደርሳል አሉ። ሃዲስ በሃሳቡ ባለመስማማታቸው አሻፈረኝ አሉ።ሃዲስ አለማየሁ ግሩም ትህትና ነበራቸው። ለዚህ ማሳያው ደግሞ ፍቅር እስከ መቃብርን የመሰለ ድንቅ ዘመን ተሻጋሪ ድርሰት ፅፈው "የአቅማቸውን ሞክረናል" ማለታቸው ነው።

ይኽ ሁሉ ሲሆን ሃዲስ አለማየሁ ብዙ መፅሐፍትን ፅፈዋል። ለአብነት ትቂቶቹን እንጥቀስ:-

1. ኢትዮጵያ ምን አይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል (1966)- ሃዲስ አለማየሁ ይኼንን መፅሐፍ የፃፉት በ1966 ዓ/ም ነው። በዚህ መፅሐፍ ሃዲስ ለሀገራችን ተገቢ ያሉትን የመንግስት አስተዳደር አይነት ጠቁመዋል። የመንግስት ለውጥን በተመለከተ እንዲህ

ይላሉ። "መቸም ለውጥ የፍጥረት ህግ ስለሆነ ዛሬ ባይሆን ነገ ለውጥ መምጣቱ አይቀርም። "ጥያቄው ለውጥ በሰላም ወይስ በደም?" የሚለውን ነው" ካሉ በኋላ " ለውጥ በሰላም ሊሆን ሲችል ለውጥ በደም እስኪሆን መጠበቅ ሁሉን ከመጉዳት በቀር ለማንም ስለማይጠቅም ለውጥ በሰላም የሚሆንበትን መንገድ አሁን ጊዜው ሳያልፍ ማበጀት አስፈላጊ ነው።"

2. ፍቅር እስከመቃብር (1958)- በዚህ ድርሰት ውስጥ የዘመኑን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር ተችተዋል። በዚህም "የቆዬ ልማድ የቆዬ በመሆኑ ሁሉ አይወድቅም÷ሁሉ አይያዝም። ጠቃሚው ይያያዛል፣ የሚሻሻለው ይሻሻላል፣ ሊሻሻል የማይችለው ይወድቃል" ሲሉ ዘመን ተሻጋሪ ምክር ይመክራሉ። ደራሲው በዚህ መፅሐፋቸው ላይ ባሳዩት ፀረ ፊውዳል ሥርዓት በደርግ አባላት ዘንድ እንደተወደዱ እና ለጠቅላይ ሚኒስትርነትም ታጭተው እንደነበረ ሻምበል ፍቅረ ሥላሴ ወግደረስ " እኛ አቢዮቱ" በተሰኘው መፅሐፋቸው ጠቅሰዋል። ሃዲስ አለማየሁም "ትዝታ" በተሰኘው መፅሐፋቸው ደርጎች ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሆኑ እንደጠየቋቸው እና እንዳልተስማሙ ፅፈዋል።

3. የልምዣት (1980)- ሃዲስ በዚህ ድርሰታቸው ብዙ አስተምረውናል። ስለ ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግን ፍልሰት እና የባእድ የባህል ወረራን አንስተዋል። ዘመናዊ ትምህርት ከባህላዊ ትምህርታችን ጋር እንዴት አዋደን መኼድ እንዳለብን፣ በዘመናዊነት ሥም ፈረንጅ አምላኪ እንዳንሆን፣ የሐገራችንን ነባር የትምህርት ሥርዓት መርሳት እንደሌለብን መክረውናል።

4. ተረት ተረት የመሰረት- በዚህ መፅሐፍ ሃዲስ አለማየሁ ብዙ ትምህርታዊ የሆኑ ተረቶችን አካትተዋል።በተለይም ስለ አይጥና ድመት በሚያወሩበት ክፍል የአውሮፓ ሃገራት ጥቁር አፍሪካውያንን ለማስተማር እና ለማሰልጠን በሚል ሰበብ የደረሰውን የመብት ረገጣ በግልፅ ያሳያል። የአውሮፓውያን በድመት ተመስለው በጥቁር ሕዝቦች ላይ የፈፀሙትን የማታለል ተግባር ያሳያል።

5. ትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም- በዚህ ሥራቸው ሃዲስ አለማየሁ ነባሩ የትምህርት ሥርዓታችን መዘመን የሚገባው መሆኑን፣ የትምህርት ይዘቱም በሐይማኖት እና በኑሮ ሥርዓት ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ የምጣኔ ሃብት፣ ፖለቲካ፣የአስተዳደር ዘይቤ፣ የኪነጥበብ እና ውትድርናን በሰፊው ቢሰጡ ሐገር ልታድግ እንደምትችል ጠቁመዋል።

6.ትዝታ (1985) - ይኼ የሃዲስ አለማየሁን የአርበኝነት እና የግዞት ዘመን ከመተረክ ባለፈ በጣሊያን ዘመን የነበረውን የውስጥ አርበኞች ትግል ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ስለእኛ ሲባል የተከፈለውን ከባድ መስዋዕትነት ለማወቅ ይኼንን መፅሐፍ ማንበብ ይመከራል።

በመጨረሻም ሐገራቸውን በአርበኝነት፣በመምህርነት፣በአምባሳደርነት፣ በሥነፅሑፍ ሥራዎች እና በተለያዩ የመንግስት የኃላፊነት ቦታዎች ሲያገለግሉ የነበሩት እኚህ የአገር አድባር ኅዳር 27 ቀን 1996 ዓ/ም ከዚህ ድካም ዓለም ተሰናበቱ። በመቃብራቸው "የተፈጥሮ ሕግ ነውና የተወለደ ሁሉ ይሞታል፣ ሰው ግን በሥራው ህያው ይሆናል፡፡" ተብሎ ተፃፈ።

ሐገራችን ኢትዮጵያ ደራሲ ሃዲስ አለማየሁን እንዴት ዘክራዋለች? በምንስ ታስታውሰዋለች?

1. ሃዲስ አለማየሁ ፍቅር እስከ መቃብርን ከፃፉ በኋላ ከኢትዮጵያውያን የልብ ወለድ ደራሲዎች የመጀመሪያው እና ብቸኛው በመሆን የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሽልማት ድርጅት ተሸላሚ ለመሆን በቅተዋል።
2. ነሐሴ 27 ቀን 1991 ዓ/ም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ድግሪ ሰጣቸው።
3. የፖስታ ቴምብር መንግስት አገሩን እና ታሪኩን ከሚያስተዋውቅባቸው መንገዶች አንዱ ነው።በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ደራሲያን ማሕበር ለሃዲስ አለማየሁ የፖስታ ቴምብር በማዘጋጀት ከ2002 ዓ/ም በኢትዮጵያ ፖስታ ድርጅት አማካኝነት ታትሞ ተሰራጭቷል። በዚህም ትውልድ ሃዲስን ሲዘክረው ይኖራል።
4. በ1999 ዓም የተመሰረተው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በምርምር እና ማሕበረሰብ አገልግሎት ተልዕኮው ለባህል እና ኪነ ጥበብ ልዩ ትኩረት እንደሚሰጥ ይታወቃል።ዩኒቨርሲቲው የተመሰረተበት አካባቢ ደግሞ የኪነ ጥበብ ሰዎች በብዛት የፈለቁበት በመሆኑ የኪነ ጥበብ አምባ ሊባል ይችላል። ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የማይነጥፈውን የኪነ ጥበብ ተሰጥዖ አጠናክሮ ለማስቀጠል በማሰብ በ2004 ዓ/ም ዩኒቨርሲቲ የባህል ጥናት ተቋም አቋቁሟል።ይኼን የባህል ጥናት ተቋም የተሰየመው የሥነ ፅሑፍ አድባር በሆኑት ሃዲስ አለማየሁ ሥም ነው። ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የባህል ጥናት ተቋም ተብሎ ይጠራል።
5. የታላላቆችን እና የሐገር ባለውለታዎችን ውለታ የማይረሳው ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብዙ አዳራሾችን በታዋቂ ሰዎች ሥም ሰይሟል። ንግስት ሳባ አዳራሽ፣

አለቃ ተክለየሱስ ዋቅጅራ አዳራሽ፣ ቀኝጌታ ዮፍታሔ ንጉሴ አዳራሽ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። ይኼ ብቻ አይደለም ዩኒቨርሲቲው አንዱን የጉባኤ አዳራሽ " ሃዲስ አለማየሁ የጉባኤ አዳራሽ" ሲል የሃገር ባለውለታ የሆኑትን ደራሲ ዘክሯል።

6. ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መጭው ትውልድ የደራሲ፣ መምህር፣ አርበኛ እና አምባሳደር ሃዲስ አለማየሁን ፈለግ እንዲከተል ለማድረግ እና ሃዲስ ለሐገራቸው ያበረከቱትን በጎ ሥራ ለመዘከር በማሰብ የመታሰቢያ ሐውልት በከተማው ውስጥ እንዲቆምላቸው አድርጓል። የመታሰቢያ ሐውልቱ ሚያዝያ 28 ቀን 2009 ዓ/ም በይፋ ተመርቋል።
7. ሃዲስ አለማየሁ ለትቂት ዓመታት ቢሆንም መምህር የነበሩ መሆኑ አይዘነጋም። ተማሪዎች የሃዲስ አለማየሁን ፈለግ ይከተሉ ዘንድ ለማስቻል በማሰብ ጎበዝ ተማሪዎች ብቻ ተመርጠው የሚማሩበት ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት የግንባታ መሰረት ድንጋይ ጥቅምት 7 ቀን 2013 ዓ/ም በደብረ ማርቆስ ከተማ ተቀምጧል። ሥያሜውም " ሃዲስ አለማየሁ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት" ተብሏል።

ምንጮች :-


1. Alemu Alene Kebebe, A short political Biography of Kibur Ato Haddis Alemayehu, African Journal of History and Culture

2. አስፋው ዳምጤ፣ የክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ የሕይወት ታሪክ፣ አጭር ማስታወሻ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና የሥነ ፅሑፍ መፅሔት

3. ዮናስ አድማሱ፣ "አስረኛንኩዋ?" ሀዲስ አለማየሁና የማህበራዊ ሂስ ስልታቸው፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና የሥነ ፅሑፍ መፅሔት

4. ሃዲስ አለማየሁ፣ ትዝታ

5. ፈቃደ አዘዘ፣ አንዳንድ ጥቅሶች ከደራሲ ሀዲስ አለማየሁ ሥራዎች፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና የሥነ ፅሑፍ መፅሔት